
# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2018 የነበረው
# የአየር ሁኔታ ግምገማ

ባለፉት አስር ቀናት ወደ ሀገራችን እየገባ የነበረዉ ዕርጥበት አዘል አየር በአብዛኛዎቹ የሀገራች አካባቢዎች ላይ ከዕለት ወደ ዕለት ተጠናክሮ ነበር የተስተዋለዉ፡፡ የነበረዉም ዕርጥበት በተለይም በዚህ ወቅት በመደበኛ ሁኔታ ደረቅማ የአየር ሁኔታ በሚያመዝንባቸዉ የሰሜን፣ የመካከለኛዉ እና የምስራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንዲኖር አስተዋፅዖ አድርጓል፡፡ በዚሁ መሰረት በብዙ ቦታዎች ላይ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደነበረ መረዳት ተችሏል፡፡ በአጠቃላይ ባለፉት አስር ቀናት የትግራይ ምስራቃዊ ክፍል፣ አብዛኛዉ አማራ፣ (ምዕራብ፣ ደቡብ እና መካከለኛዉ ኦሮሚያ)፣ የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል፣ ደቡብ አፋር፣ ጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ እና አንዳንድ የምስራቅ ኢትዮጵያ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ በተጨማሪም አልፎ አልፎ ከነበረዉ ጠንካራ የደመና ክምችት በአንዳንድ ቦታዎች ላይ ከባድ መጠን ያለዉ ዝናብ ተመዝግቧል፡፡ ለመጥቀስም በአርባ ምንጭ 53.0፣ በዳንግላ 32.4፣ በዲላ 32.4፣ በመተማ 41.5፣ በመካነሰላም 51.7፣ በሰኮሩ 30.2፣ በሻምቡ 39.0፣ በቢሾፍቱ 48.0፣ በኢጃጂ 41.3፣ በፍሬወይኒ 32.2፣ በአዴት 60.5፣ በነቀምቴ 57.4፣ በሆሳና 35.8 እና 31.4፣ በሊሙገነት 48.0 እና በጅማ 36.2 በሚ.ሜ ይገኙበታል


ባለፉት አስር ቀናት የዝናብ መጠን ከሀገሪቱ ቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም በሰሜንና ደቡብ ጎንደር፣ በምዕራብ እና ምስራቅ ጎጃም፣ በሰሜን ወሎ እና ዋግህምራ፣ በአሶሳ እና በከማሽ፣ በምስራቅ ትግራይ፣ በሁሉም የወለጋ ዞኖች፣ በኢሉባቦር እና ጅማ፣ በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ዞኖች፣ በሁሉም የደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል ዞኖች፣ በጉጂ እና በጥቂት የቦረና ዞን ላይ ከ25-106 ሚ.ሜ የሚደርስ ከ4-7 ቀናት ያህል ዝናብ የነበራቸዉ ሲሆን፤ በጋምቤላ ዞኖች፣ በደቡብ ወሎ፣ በሰሜን ሸዋ(03)፣ በአርሲ እና ባሌ፣ በምስራቅ እና ምዕራብ ሀረርጌ፣ በምስራቅ ሸዋ፣ በአፋር ክልል ዞን 03፣ 04 እና 05 ላይም ከ5-24 ሚ.ሜ ከ3 ላነሱ ቀናት ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡) ።

ባለፉት አስር ቀናት የዘነበው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር ሲነፃፀር በትግራይ፣ በአማራ፣ በቤንሻጉል-ጉሙዝ፣ በጋምቤላ፣ በደቡብ ብሄር ብሄረሰቦች እና ህዝቦች ክልል የሚገኙ ዞኖች፣ በወለጋ እና በሸዋ፣ በጉጂ እና ቦረና፣ በአፋር ክልል ዞን 02፣ 03፣ 04 እና 05 እንዲሁም በሲቲ ዞኖች ላይ መደበኛ እና ከመደበኛ በላይ የሆነ ዝናብ ስርጭት የነበራቸዉ ሲሆን፤ የተቀሩት አካባቢዎች ላይ ከመደበኛ በታች የሆነ ዝናብ ተመዝግቧል (ካርታ 3) ።


ካርታ1   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ



ካርታ2   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸው ቀናት ብዛት



ካርታ3   እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን ከመደበኛው ጋር በመቶኛ ሲነፃፀር




# <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

# <u>በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

ባሳለፍነው የኖቨምበር የመጀመሪያዎቹ አስር ቀናት ወቅቱን ካልጠበቀ ዝናብ ጋር ተያይዞ በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ እርጥበታማው ሁኔታ ተጠናክሮ እንደነበረ የተተነተኑ የአግሮሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በተለይም በመደበኛ ሁኔታ ደረቃማው የአየር ሁኔታ በሚስተዋልባቸው የሰሜን፣ የምስራቅና የመካከለኛው የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ የተጠናከረ እርጥበት እንደነበረ መረዳት ተችሏል፡፡ ይህም ሁኔታ በተለይም የመኸር ሰብል ሙሉ በሙሉ በደረሰባቸውና የሰብል ስብሰባና ድህረ ሰብል ስብሰባ እየተከናወነ በሚገኝባቸው አካባቢዎች የነበረው ወቅቱን ያልተበቀ እርጥበት በአንዳንድ ሰብሎች ላይ ጉዳጥ እንዳስከተለ ይገመታል፡፡ በተጨማሪም ከማሳዎች መጨቅየት ጋር ተያይዞ በእንዳንድ አካባቢዎች ላይ በሚገኙ የመንግስትም ይሁን የግል እርሻዎች በማሽን እገዛ ሰብሎችን ለመሰብሰብ የሚደረገውን ጥረትም አስቸጋሪ አድርጎት እንደነበረ ግምት መውሰድ ይቻላል፡፡ እንዲሁም የነበረው እርጥበታማ ሁኔታ ለእንዳንድ የሰብል ተባዮችና በሽታዎች መከሰት ምቹ እንደነበረ ይገመታል፡፡ በሌላ መልኩ በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው በሆኑት አካባቢዎች ለሚገኙት ሰብሎችም ሆነ ቋሚ ተክሎች እንዲሁም በአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ላይ የተገኘው እርጥበት ለመጠጥ ውሀና ለግጦሽ ሳር አቅርቦት ገንቢ ሚና ነበረው (ካርታ 4)፡፡

ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1 እስከ 10/2018 ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ




# <u>እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ</u>

## <u>በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተጽዕኖ</u>

እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1-10/2018 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ እንቅስቃሴ ላይ የነበረው ገፅታ በተመለከተ የተሻለ የእርጥበት መጠን በሀገሪቱ ደቡብ፣ ደቡብ ምዕራብና የሰሜን ምዕራብ ዳርቻ ባሉ የታችኛው ተፋሰሶች ላይ መጠነኛ እርጥበት ከመስተዋሉ በስተቀር በአብዛኛዎቹ ተፋሰሶች ላይ ደረቅ ሁኔታ አመዝኖ ተስተዉሏል$ ይህንን ተከትሎ በጥቂት የላይኛውና የታችኛው ገናሌዳዋ፣ የላይኛውና መካከለኛው ኦሞጊቤ፣ ጥቂት የላይኛው አባይ፣ ተከዜ እና መካከለኛው ስምጥሸለቆ አዋሳኝ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ የእርጥበት ሁኔታ የተገኘ ሲሆን፤ በምስራቃዊ ባሮአኮቦ፣ በጥቂት የታችኛው አባይ፣ በአብዛኛዉ ተከዜ፣ በታችኛው ኦሞጊቤ፣ በጥቂት የመካከለኛውና የታችኛው ገሌዳዋና ስምጥ ሸለቆ እንዲሁም አዋሳኝ ተፋሰሶች መጠነኛ እርጥበት አግኝተዋል$ በተቀሩት የሰሜን ምስራቅ፣ አብዛኛው የምስራቅና የደቡብ ምስራቅ ተፋሰሶች ላይ የበጋው ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ ተስተውሏል (ካርታ 5)$

ካርታ 5. እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 1- 10/2018 በተፋሰሶች ላይ የነበረው የእርጥበት መጠን



# እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2018 የሚኖረው

# የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቨምበር ሁለተኛው አሥር ቀናት  በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ የሚያመዝን ሲሆን፤ ከዚሁ ጋር ተያይዞ በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ ደጋማ ቦታዎች ላይ የሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ይዘወተራል፡፡ በሌላ በኩል የደቡብ ምዕራብ፣ የደቡብ እና የደቡብ ምሥራቅ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡

በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምክንያት የሚሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አልፎ አልፎ ባሉት ቀናት ሊጠናከሩ እንደሚችሉና በከባቢው አየር ውስጥ የእርጥበት መጨመር ሊያስከትሉ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ። ስለሆነም ቀደም ባሉት ቀናት በአንዳንድ አካባቢዎች የተስተዋለው ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ከሞላ ጎደል ቀጣይነት ሊኖረው እንደሚችል የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ።

በአጠቃላይ በመጪዎቹ አሥር ቀናት የበጋው ደረቃማ የአየር ሁኔታ አመዝኖ እንደሚቆይ የሚጠበቅ ቢሆንም፤ ወቅታቸው ባልሆኑት በጥቂት የሰሜን አጋማሽ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ ሊኖር ይችላል። ከተተነበዩ የአየር ሁኔታ መረጃዎች መረዳት እንደሚቻለው በተለይም በደቡባዊው የሀገሪቱ አጋማሽ ላይ ዝናቡ የተጠናከረ  ሊሆን እንደሚችል ይጠበቃል።

<u>በሚቀጥሉት አሥር ቀናት ከትግራይ ክልል የምሥራቅና የደቡብ ትግራይ ዞኖች፤ ከአማራ ክልል የሰሜንና የደቡብ ወሎ፣ ባህርዳር ዙሪያ፣ ከኦሮሚያ ምዕራብና ምሥራቅ ወለጋ፣ ጅማ፣ ኢሉአባቦራ፣ ምዕራብና ምሥራቅ ሐረርጌ፣ ድሬዳዋና ሐረር፣ አርሲ እና ባሌ፣ የጉጂ እና የቦረና ዞኖች፤ አዲስ አበባ፤ ጋምቤላ፤  ከቤንሻንጉል ክልል የአሶሳና የከማሺ ዞኖች፤ ከደቡብ ብሄር ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ደግሞ የወላይታ፣ የዳውሮ፣ የጋሞጎፋ፣ የከፋና የቤንች ማጂ፣ የደቡብ  ኦሞ እና የሰገንሕዝቦች፤ በሶማሌ ክልል የሚገኙት የደገሀቡር፣ የፊቅ፣ የሊበን፣ የአፍዴር፣ የፋፈን፣ የሲቲ እና የጎዴ ዞኖች በአንዳንድ ሥፍራዎቻቸው ላይ ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ። የተቀሩት የሀገሪቱ ሥፍራዎች በአብዛኛው ደረቅ ሆነው ይቆያሉ።</u>

## እ.ኤ.አ. ከኖቬምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በእርሻው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተጽዕኖ

በመደበኛ ሁኔታ በኖቬምበር ሁለተኛ አስር ቀናት በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቃማ የእርጥበት ሁኔታ የሚያመዝን ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አብዛኛዎቹ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች በሰብል ስብሰባና የድህረ ሰብል ስብሰባ እንቅስቃሴ ወጥ የሚሆኑበት ጊዜ ነው፡፡ በተጨማሪም በአንዳንድ ደጋማ አካባቢዎች ላይ ሌሊቱና የማለዳው ቅዝቃዜ ጠንከር የሚልበት ጊዜ ነው፡፡

በተሰጠው የአስር ቀን የአየር ሁኔታ ትንበያ መሠረት በያዝነው የኖቬምበር ሁለተኛው አስር ቀናት ዉስጥ አልፎ አልፎ ወቅቱን ያልጠበቀ ዝናብ እንደሚኖር የተተነበዩ የሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች አመልክተዋል፡፡ በተለይም በትንበያው ላይ የተጠቀሱት ዞኖች ከዝቅተኛ እስከ መካከለኛ ደረጃ የሚደርስ የእርጥበት ሁኔታ ሊኖራቸው እንደሚችል ተመልክቷል፡፡ ይህም ሁኔታ ወቅቱን ያልጠበቀ የእርጥበት መጠናከር የመኸር ሰብሎችን ለሚሰበስብና የድህረ ሰብል ስብሰባ ለማከናወን አስቸጋሪ ሁኔታ ሊፈጥር ይችላል፡፡ በተለይም በሰሜን፣ በምስራቅና በመካከለኛው የሀገሪቱ የመኸር ሰብል አብቃይ አካባቢዎች ላይ በአሁኑ ሰዓት የተለያዩ ሰብሎች በመድረቅና በመሰብሰብ ላይ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ ወቅታዊ ያልሆነው እርጥበት ሙሉ ለሙሉ በደረሱና በማሳ ላይም ሆነ በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ በሚገኙ ሰብሎች ላይ ጉዳት እንደሚያደርስ ይገመታል፡፡ በመሆኑም አርሶ አደሮችም ሆኑ የሚመለከታቸው አካላት ልዩ ትኩረት በመስጠት አስፈላጊውን ርበርብ በማድረግ የደረሱ ሰብሎችን መሰብሰብና በአግባቡ የመከመር ተግባራትን ለማከናወን ከወዲሁ አስፈላጊውን እርምጃና ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ይመከራሉ፡፡ በተጓዳኝም እርጥበቱ እንደ ዋግ ያሉ የሰብል በሽታዎችን እንዲፈጠሩ ምቹ ሊሆን እንደሚችል ከግምት በማስገባት ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል፡፡ በሌላ መልኩ በደቡብ አጋማሽ ላይ እንደሚጠናከር የሚጠበቀው የእርጥበት ሁኔታ በተለይም በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸው ለሆኑት የአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች ለሚገኙ የበጋ ወቅት ሰብሎች ቋሚ ተክሎች እንዲሁም ለግጦሽ ሳርና ለመጠጥ ውሀ አቅርቦት አዎንታዊ ጎን ይኖረዋል፡፡

## እ.ኤ.አ ከኖቬምበር 11-20/2018 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ በውሃው ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት አስርት ቀናት የበጋው ደረቅ የአየር ሁኔታ አመዝኖ የሚቆይ ቢሆንም፤ በደቡባዊ የሀገሪቱ ክፍሎች በሚገኙ ተፋሰሶች ላይ የተሻለ ዝናብ ሊኖር እንደሚችል የትንበያ መረጃችን ያመለክታል፡፡

በዚሁ መሰረት ጥቂት የላይኛው ተከዜ፣ አብዛኛው አባይ፣ ባሮ አኮቦ፣ መካከለኛውና የታችኛው ኦሞ ጊቤና የስምጥ ሸለቆ፣ የላይኛው አዋሽ፣ ገናሌ ዳዋ፣ የላይኛውና የታችኛው ዋቢሸበሌ፣ የላይኛው የኦጋዴን ተፋሰሶች ከቀላል እስከ መካከለኛ መጠን ያለው ዝናብ ሊያገኙ እንደሚችሉ የትንበያ መረጃዎች ያመለክታል፡፡ ይህም ሁኔታ የበጋው ዝናብ ተጠቃሚ ተፋሰሶች ላይ ጥሩ የውሃ ሀብት እንዲያገኙ የሚረዳ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ የሚገኘውን ውሃ ተጠቃሚዎች በአግባቡ እንዲጠቀሙ እናሳስባለን፡፡ የተቀሩት የሀገሪቱ ተፋሰስ ክፍሎች በደረቃማው የአየር ሁኔታ ላይ ይቆያሉ፡፡